# ትግላችን ዜና

ዓለም-አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ሕብረት



በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board
P.O.Box 3198, 10364 Stockholm,3
SWEDEN


# በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ፲፫ኛ ጠቅላላ ጉባኤ የፖለቲካ ውሳኔ


መስከረም 1976 ቅጽ 11 – ልዩ እትም

## የዘውዱ አገዛዝ የተደመሰሰበት 9ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ከአኢተማ ሥ/አ/ኮሚቴ የወጣ መግለጫ

በየካቲት ወር 1966 ዓ.ም ገደማ አንድ ያልታሰበ ማዕበል በኢትዮጵያ ምድር ላይ ማንዣበብ ጀመረ ። ጀንበር ወጥታ በጠለቀች ቁጥር ማዕበሉ በሚያርፍበት አካባቢ ጭንቀትና ጥበት ሰፈነ፣ መሬት ቆና አየሆነች መጣች ። ይህ ማዕበል ከሰማይ የወረደ ከተራራ ወይም ከገደል የፈለሰ ባይሆን አንድ ሌላ ቁጣ ነበር ። የሕዝብ ቁጣ — የአብዮት ማዕበል ።

ማዕበሉ የመንፈቅ ጉዞውን አጠናቅቆ በመስከረም 2 ቀን 1975 ዓ.ም የኢትዮጵያን ሕዝብ ለረጅም ዘመን በፈላጭ ቆራጭነት ይገዛ በነበረው የባላባት ገዢ ቁንጮ ላይ ሲያርፍ፣ በስንት አውታር ተጠግኖ የኖረው የዘውዱ አገዛዝ ተንኮታኩቶ አንዲፈርስ አደረገው ።

በዚህ የዘውዱ ጥላ ሥር ተጠልለው የነበሩ አፋሽ አጎንባሾች አለሁላህ ባዮች የውጭ አቃንቃኞች ጭምር ይህን የሕዝብ ቁጣና የአብዮት ማዕበል አሰፈው በቅጽበት ለምትቆጠር ጊዜ እንኳን ዕድሜአቸውን ማራዘም ባይችሉ ቀሩ ።

በቤተ መንግሥት፣ በአገር፣ በወገንና በወዳጅ አካባቢ ቆይታ ተሰማ፤ ከወፎች ጨጨታነት ለማለፍ ባይችል ቀረ ። በሰፊው ሕዝብ መንደር ዕልልታ ቀጠለ፤ ፍስሐና ደስታ ሰፈነ ። ሰፊው ሕዝብ የአኔ ከሚላቸው ታላላቅ በአላት ተወዳዳሪ የሌለውን ታሪካዊ ዕለት መስከረም ሁለትን በማይፋቅ ቀለም በታሪክ ምዕራፎች ውስጥ አሰፈረ ። በዚህ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ የአዲስ ሕይወት፤ የአዲስ ዓለም ጥርጊያ ጉዳና መታየት ጀመረ ። ተንኮታኩቶ በወደቀው የዘውዱ አገዛዝ መቃብር ላይ፣ የሕዝባዊ ሥልጣንን ሐውልት ለመትከል የሚደረገው ዝግጅት ባይውል ባያድር መፋፋም ጀመረ፤ በከተማ፣ በገጠር፣ በቀሳና በደጋው የአዲሲቱ ኢትዮጵያ የተስፋ ጮራ ፈነጠቀ ። የነጻነት የእኩልነት የዲሞክራሲ ጮራ !

ይህ የተስፋ ጮራ የጨለማውን ጨዛ አርግፎ የሰፊውን ሕዝብ ተሳትፎ የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የምትመሰረትበትን አቅጣጫ የሚያሳየውን የችቦ መብራት አያውለበለበ፤ በደመቀ ብርሃን አብዮት ወይም ሞት እያለ ሰፊው ሕዝብ ለረጅም ትግል ጉዞውን የጀመረው ከዚህ ዕለት በኋላ ነበር ፡፡ የዘረፋውን አያድርገውና በዝቀታቾ የመጀመሪያ ጥቂት ዓመታት ሰፊው ሕዝብ የተቀዳጃቸው ድሎች ገሚሶቹ ቢኮላሹም፤ ጠላት በቀላሉ ሊደመስሳቸው የማይችል ድሎች ደግሞ አሉ ወደፊትም ይኖራሉ ፡፡

ባጭሩ መስከረም ሁለት ይህን ታሪካዊ መልኩን እንደያዘ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍና ሲታሰብ ይኖራል ፡፡ ዛሬም ለ9ኛ ጊዜ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብና አኢተማ ይህንን ዕለት ሲያስቡት ይህንኑ ታሪካዊ ጠባይ በማስታወስ ቢሆንም፤በመስከረም 2 ቀን 1974 ዓ.ም ከባላባታዊ አገዛዝ እጅ ተፈልቅቆ የወጣችውን ሥልጣን ለመረከብ ሰፊው ሕዝብ ድርጅትና ትጥቅ ስላልነበረው፤ በጊዜው ታጥቆ ለነበረው ወታደራዊ ድርጅት መልቀቁ በመገደዱና፤ በመስከረም 2 ቀን 1974 ዓ.ም የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ የተነደፉት የነጻነት፤ የእኩልነትና የዲሞክራሲ ተስፋዎች ማረጋገጫ የሆነው የሕዝብ ሥልጣን ዛሬም ባይረጋገጥ አለ ፡፡

" ፍሉ የሚበላ ሲሄድ፤ልጋም የሚበላ መጣ " እንዲሉ፤ዛሬ 9ኛው ዓመት ሲታሰብ ፤ የፋሺያ መንግሥት አሸንጉሊት የሆነው የኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ፈላጭ ቆራጭ መንግሥት በአንዳንድ ሁኔታዎች የባላባታዊ አገዛዙ ይፈጽማቸው ከነበሩ የጭካኔና፤ የአረመኔነት በብዙ እጅ የከፋ በደል በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እያደረሰ እንደሆነና የሀገሪቱን ብሔራዊ ነጻነትም አባልፍ የሸጠ ባለጌ መንግሥት መሆኑ ማስብ እንገደዳለን ፡፡

ስለሆነም፤የሁለተኛው የካቲት 1966ዓ.ም ፤ ሁለተኛው መስከረም ሁለት 1974 ዓ.ም የአብዮት ማዕበል፤ ደመና በአራቱ ማዕዘን የኢትዮጵያ ክፍሎች ቪበብ ጀምሯል ፡፡ ይህ ማዕበልም በዚህ ፈላጭ ቆራጭ መንግሥት ጭዳነት ያከትማል ፡፡ የሰፊው ሕዝብ ትግል ያሸንፋል ፡፡

THE ETHIOPIAN STUDENTS UNION IN EUROPE

ማሳሰቢያ
በ1966 የሚለው በኢ.አ. ነው ፡፡
በ1974 የሚለው በአ.አ. ነው ፡፡

ለብሔራዊ ነጻነት ተፋርጋሪዎች
ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች አገር ወዳዶች
በጠቅላላው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝቦች
የመስከረም ሁለት አርበኞች
ከንዳችሁን በጋራ ጠላት ላይ አስተባበሩ
ድል የሕዝብ ነው !!



## መግቢያ

በአውሮፖ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር 23ኛ ጠ/ ጉባዔ ከ1/8/83 እስከ 4/8/83 ድረስ በምዕራብ በርሊን ከተማ በአብዮታዊና በጋለ መንፈስ ተካሂዷል ፡፡

ይህ ጉባዔ የተካሄደው፤ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አሁንም በወታደሩ የፈላጭ ቆራጭ መንግሥትና ገበረአበሮቹ የፍዳን ጽዋ እየተቀበሉ፤ ለሌላ አስቃቂ ረሃብ በተጋለጡበትና በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ወደሞት አፋፍ ላይ በተወረወረበት ወቅት ነው ፡፡

በዚህ ጉባዔ ላይ ማኅበራችን የኢትዮጵያን ጊዜያዊ ሁኔታ ብቻ ባይሆን፤ ማኅበሩ ባለፉት ዓመታት ያደረገውን ትግል በጊዜ በጊዜ ከሩፍሉ ዲሞክራሲያዊና ጓዳዊ ውይይቶች ካካሄደ በኋላ፤ ጊዜውና ሁኔታዎች ለሚጠይቁትና በየጊዜው ለሚወለዱት አዳዲስ ነገሮች ብቁ ሆኖ መገኘት እንዳለበት በማመን፤ ለወደፊት የትግል ጉዞ የሚበጁትን አዳዲስ መንገዶች ቀይሷል ፡፡

በጉባዔው መጀመሪያ ዕለት የሥ፡ አ/ኮሚቴና የመጽሔት ቦርዱ ስለ ኢትዮጵያና ስለ ዓለም አቀፍ ሁኔታ የመክፈቻ ንግግርና መግለጫ ከሰጡ በኋላ፤ ቤቱ ጉባዔውን የሚመሩ ሊቀመንበርና ጸሐፊዎች በመምረጥ መደበኛው ጉባዔ ተጀመረ ፡፡በዚህም መሠረት በዚህ ዕለት የሥ/አ/ኮሚቴና የመጽሔት ቦርዱ 1982/83 ዓ.ም የሥራ ዘመን ስለ አከናወኗቸው ተግባሮች ሪፖርት አቅርበዋል ፡፡ ቤቱም በሪፖርቱ ላይ ሰፊ ውይይት ካካሄደ በኋላ በሙሉ ድምፅ ተቀብሎት አጸልፍአል ፡፡ በዚህ ዕለት ቀ/ማኅበራት የሠሯቸውን ሥራዎች በሪፖርት መልክ አቅርበዋል ፡፡

የማኅበራችንን 23ኛ ጉባዔ ምክንያት በማድረግ ከልዩ ልዩ ተራማጅና ዲሞክራቲክ ድርጅቶች የተላከ የአጋርነት መግለጫ ተነቧል ፡፡

የአጋርነት መግለጫ የላኩ ድርጅቶች የሚከተሉት ናቸው ፡፡

1ኛ የመላ ኢትዮጵያ በሻሊስት ንቅናቄ /መኢሶን/
2ኛ. የተባበሩት ተራማጅ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች አንድነት ማኅበር በሰሜን አሜሪካ
3ኛ የእንግሊዝ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የጥናት ክበብ

4ኛ የሆላንድ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የጥናት ክበብ
5ኛ የቤልጅግ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ቅ/ማኅበር
6ኛ ከፀረ- ኒዉክሊሳር እንቅስቃሴ / እንግሊዝ አገር /

ጉባኤ፣ የሀገሪቱን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የሚሊተሪና የማኅበራዊ ሁኔታዎችን በተከታታይ ለሁለት ቀናት ካጠናና ከተወያየ በኋላ፣ ውሳኔውን ለማርቀቅ በተመረጡት [illegible] ጓዶች አማካይነት፣ በ4/8/83 ቤቱ በቀረበው ውሳኔ ላይ እንደገና ተወያይቶ፣ ውሳኔውን ካለምንም ተቃውሞ በሙሉ ድምፅ አሳልፏል ::



## የ23ኛው ጠቅላላ ጉባኤ የጥናት አርእስት

1. የኢሲተማ ሚና ጥንካሬና ድክመት
   1.1 እስከ 1974 ዓ.ም ድረስ
   1.2 ከ1974-1977 ድረስ
   1.3 ከ1977 ጀምሮ እስከአሁን ድረስ
2. የኢትዮጵያ ህብረተሰብ መደቦችና ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች
   2.1 መንግሥትና ህዝብ
   2.2 ኢሠፓአኮ፣ የወታደሩ መንግሥት፣ ቢሮክራሲውና የመንግሥቱ ኃይለማርያም ሚና
   2.3 የአገሪቱ ቀሬኔ አቀማመጥና አፈታት
3. የዛሬይቱ ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሥርአትና የማህበራዊ ሁኔታ
   3.1 የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ልዩ ልዩ መልኮችና ጠባዮች
   3.2 የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መሠረታዊ ችግሮች
   3.3 የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ጊዜያዊ ችግርና ረሃብ
4. የውጭ ሀይሎች ሚና በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ
   4.1 ሶቭየትህብረትና ሌሎች ምሥራቅ አውሮፓ አገሮች
   4.2 አሜሪካና ምእራብ አውፓ
   4.3 የጐረቤት አገሮች
5. የብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄ፣የፓርቲና የግምባር ጥያቄ
   5.1 የብሔር/ብሔረሰብ ችግርና አፈታት
   5.2 የአገረ ሰቆቄ ፓርቲ ጥያቄ
   5.3 የግምባር ጥያቄና የድርጅት ሁኔታ
   5.4 የህዝባዊ ሀይሎች ሚና

## የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ

አምባገነኑ የወታደር መንግሥት ከ1977 ዓ.ም ወዲህ፣ በሀገራችን ላይ ትምክሕተኛነት የተመሳበትን ጦርነት በማወጁና ሕዝባችንን በዚህ የእርስ በእርስ ጦርነት የተነሳ እንዲሰደዱ በማድረጉ፣ የሕዝቡን ሰብአዊ መብት በመርገጥ፣ የፈላጭ ቆራጭ አገዛዙን አስፍኖ ይገኛል :: ለዚህ ትምክህተኛ ጦርነትና የበላይነቱንም እንደተቀዳጀ ለመቆየት ባለው ፍላጎት፣ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮች አሰልፏል :: የሚቃናቀኑትንም ኃይሎች ቀስ በቀስ ከመታና ከጨፈጨፈ በኋላ የቀሩትን የሱ ታዛዥ በማድረግ የበላይነቱን አረጋግጦ ሕዝባችንን ፍዳ ውስጥ የከተተ ጸረ ዲሞክራቲክና ጸረ ሕዝብ መንግሥት ነው ::

በዚህ አገዛዝ ቁንጮ ላይ መንግሥቱ ኃይለማርያም ወሳኙ ሚናን በመጫወት፣ አንዱን በአንዱ እያስፈራራ፣ ሌላውን እያቀረበ እየሸመና እየሻረ፣ በአጥፊ የከፋፍለህ ግዛውን ጨዋታ እየተጫወተ የበላይነቱን በግልጽ አረጋግጦ ይገኛል :: ባለፉት ጊዜያት በተከታታይ የተደረገው ሹም ሽር፣ ሹማምንቱን እንደፈለገው በማፍረጥና በማንሳት፣ ከቦታ ቦታ በማዘዋወርና በሌላ በመተካት የወደደው የማንአለብኝነትና የንቀት ተግባር፣ መንግሥቱ ኃይለማርያም የቱን ያህል በሹማምንቱ ላይ የበላይነቱን የተቀዳጀ መሆኑን የሚያሳዩ በቂ ምስክሮች ናቸው :: በሌላ ወገን፣ አሁን የሚቃናቀን ኃይል እንደሌለ የተሸመተም ሆነ የተሻሩት ለእሱ እየሰገዱና የሱን የበላይነት አሜን ብለው ተቀብለው የሚኖሩ መሆናቸውን ያመለክታል :: ይህ፣ መንግሥቱ ኃይለማርያም የተቀዳጀው ናበላይነት በቢሮክራሲውና በቴክኖክራቶች ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በእሱ አካባቢ ባሉና አሁን ቀደም ብለው በሚቀናቀኑ የደርግ አባሎች ላይም እንደሆነ ከተደረገው ናሹም ሽር ሆነ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ለመረዳት ይቻላል ::

ከዚህ በተረፈ፣ ይህ የመንግሥቱ ኃይለማርያም አርምጃ ሌሎች ሁለት ነገሮችንም በማሰብ የተወሰደ እንደሆነ መገመት ከባድ አይሆንም :: በአንዱ በኩል፣



ለቴክኖክራቶች ሹመት በመስጠት የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመፍታት የሚችል ስለመሰለው ነው :: በሌላ ወገን፣ በየሚኒስቴሩ መ/ቤቶችና በየአካባቢያቸው የተጠሉ ሹማምንትን በማስወገዱና በመለዋወጥ ተወዳጅነትን ለማትረፍ በመፈለጉም ነው :: " አሳቸው ምን አደረጉ ሚኒስተሮቻቸው ናቸው እንጂ " የሚለውን የዱሮውን የንጉሣዊ አገዛዝ ሰበካ በሕዝቡ ውስጥ ለማስረፋት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው :: በዚህም ከደርግና ከቢሮክራሲው ወጪ ሌላ የኅብረተሰብ ክፍልን ተሸካሚው ኃይል ለማድረግ ይሞክራል ::በዚህ መልክ፣ የሥልጣን ዘመኑን አርዝሞ ለመቆየት ከፍተኛ ሙከራ እያደረገ ነው ::

ይሁንናም፣ ይህ ሁኔታ በፖለቲካው መዋቅር አካባቢ በቀላሉ የሚፈረክስ ኃይል እንዳለ ለማወቅ በፍጹም ከባድ አይሆንም :: ሹማምንቱ የመንግሥቱ ኃይለማርያምን የበላይነት ይቀበሉ እንጂ፣ ዛሬ ሀገሪቱን የተበተባትን የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የፖለቲካ ችግሮች ሊወጧቸው በፍጹም እንደማይችሉና ለዚህም ችሎታ እንደሌላቸው ለማወቅ ሲቻል፣ ከችግሩም ጥልቀት የተነሳ " አኔ የለሁበት " ከደሙ ንጹሕ ነኝ " በሚል ከኃላፊነት ለመሸሽ ትልቅ ሙከራ እያደረጉ መሆናቸው የታወቀ ነገር ነው :: እንግዲህ በአገዛዙ ላይ የሕዝባዊ አመጽ እያስገመገመ ሲመጣ፣ ሹማምንቱ ከዚህ አገዛዝ ጋር በቀላሉ አብረው እንደማይነጉዱ ለማወቅም አስቸጋሪ አይሆንም ::በሌላ ወገን ገን፣ እነዚህ ሹማምንቶች ከኃላፊነት ለመሸሽ የሚጥሩትን ያህል በዚህም በዚያም ተስገብግበው፣ " ዛሬ በልቶ ሰሙት " በሚል ፈሊጥ ካለው አገዛዝ ጋር ሆነው ሕዝባችንን በማራቆትና ፍዳ በማሳየት የሚጫወቱት ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም ::

አምባገነኑ የወታደር መንግሥት በሕዝባችን ላይ ትምክሕተኛ ጦርነትን ለማካሄዱ የሚጠቀመው ሀብት በሀገሪቱ ውስጥ የሚመረተውን የእርሻም ሆነ የኢንዱስትሪ ውጤት እንዲሁም ለአገልግሎት የሚውሉ ነገሮችን፣ / ትራንስፖርት፣ሕክምና ወዘተ / የመሳሰሉትን ከሰፊው ሕዝብ ዘንድ በጉልበት እየመጠጠ በመውሰዱ ነው :: በዚህም፣ በአንዱ በኩል የሀገሪቱን ሀብት ጠቃሚ /ፕሮዳክቲቭ/ ባልሆነ

ቦታ ላይ ሲያውል፣ በሌላ በኩል ሕዝባችንን አራቍቶና አደኽይቶ ይገኛል ። በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር ወታደርም በማሰለፍና በየቦታው በማዘመት የሕዝቡን ተግባር ወደ ጦር ትግል እንዲያተኩር አድርጎታል ። በመሆኑም፣ የዛሬው አገዛዝ ጠባይ የሕዝቡን ተግባር ወደ ትምክሕተኛ ጦርነት ላይ እንዲያተኩር ያደረገና ለዚህም የኅብረተሰቡን ሀብት እየዘረፈ ለዚህ ሕዝብ አስጠራሽ ጦርነት የሚያውል መንግሥት ነው ብንል ስህተት አይሆንም ።

የዛሬው አገዛዝ፣ ይህንን ትምክህተኛ ጦርነት ለማካሄድ ከውስጥ ቢሮክራሲውንና ሌሎች ለጥቅማቸው የአደሩ አጉብዳጅ ኃይሎች ሲተባበሩት፣ ከውጪ ደግሞ በገፍ መሣሪያ በማቀበልና በማማከር የሩሲያ መንግሥትና ተቀጥያዎቿ በዚህ የእርስ በእርስ ጦርነት ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ነው ። በዚህም የቦሽየት ኅብረት በገፍ ለምታመርተው የጦር መሣሪያ ትልቅ የሕዝብ ማለቂያ ገበያ ስታገኝ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሀገሪቱን የጦር መሣሪያዎቿ መለማመጃ መድረክ አድርጋ በቀጥታ ሥር ለማድረግ በቃታለች ። በዚህም ተግባሯ፣ የቧን የበላይነት ከሚቀበልና ጥቅሟን ከሚጠብቅ ማንኛውም ጸረ ሕዝብና ፋሽሽት ኃይል ጋር እንደምትተባበር ስታስመስክር፣ በሌላ ወገን ደግሞ የቧን የበላይነት አልቀበልም የሚሉትን ኃይል ለማጥፋት እንደምትምክር ነው ። በመሆኑም፣ በሕዝባችን ላይ ካለው አገዛዝ ጋር በመተባበር የፈጸመችው ግፍ ከኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በቀላሉ ሊፋቅ የሚችል አይደለም ። የሩሲያ መንግሥት፣ በዚህ ተግባሯ በተጨማሪ ያስመሰከረችው፣ የመንግሥቷን ፀረ አብዮት፣ ፀረ ሕዝብ፣ ፀረ ዲሞክራሲና ከዚህም የተነሳ ሕዝብን በመናቅ ከረጅም ጊዜ አንጻር አርቆ ኅብረተሰብአዊ የታሪክ ሂደትን ለመገመት እንደማትችል ነው ። ሁሉንም ነገር በጉልበትና በአለኝ ኃይል ለመደምሰስ እችላለሁ የምትል፣ ልክ እንደሌሎቹ ፀረ አብዮት ኃሎች የምታስብ ፀረ አብዮት መንግሥት ነች ።

የዛሬው የወታደር መንግሥት የጭቆና አገዛዙን ለማርዘም የሕዝቡን መብት ባለው ኃይል ሁሉ ረግጦ እንደሚገዛ ተደጋግሞ የተነገረ ሀቅ ነው ። የስለላ መረቡን ዘርግቶ ሕዝባችንን ፍዳ ውስጥ ከቶታል ። ከዚህም የተነሳ ሕዝባችን ከፍ



ተኛ የሀሊና መጭዝቅ ደርሶበት በሽብር፣ በመፈራራት፣ እርስ በእርስ ባለመተማመን እንዲኖር ተገዷል ። ሰፊው ሕዝብ የኅብረተሰብ ክፍልና ልዩ ልዩ መደቦች፣ ማለትም፣ ምሁሩ፣ የቢሮ ሠራተኛው ፣ በየጦር ሜዳው ደሙን በከንቱ የሚያፈሰው ሠራዊት፣ ተማሪው የወዝ አደሩ መደብ፣ አርሶ አደሩ፣ ሰፊው የንዑስ ከበርቴ መደብ... ወዘተ፣ በዚህ አገዛዝ፣ በቢሮክራሲውና ጥቂት ለጥቅማቸው በአደሩና በውጭ ኃይሎች ተባባሪነትና አማካሪነት የስቃይ ጽዋን እየተቀበሉ ነው ። በመሆኑም፣ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ዋና ቅራኔ በአንድ በኩል ከላይ በተጠቀሱት ሰፊ የኅብረተሰብ ክፍልና መደቦች ሲሆን፣ በሌላ ወገን ደግሞ፣ ዲሞክራሲን በማፈን፣ ብሔራዊ ነጻነትን በማስደፈርና በመርገጥ፣ የብሔር/ብሔረሰቦችን መብት በመርገጥ፣ ሰላምን በማደፍረስ... ወዘተ አንድ ላይ በመቀላለፍ ሕዝባችንን ስቃይ በሚያባዑት ጥቂት ከሃዲ የገዢው መደቦችና ተባባሪዎቻቸው እንዲሁም የሩሲያ ተስፋፊ መንግሥትና ገብረአበሮቻቸው መሀከል ነው ።

ይህ 23ኛው የአኢተማ ጠ/ጉባዔ ከዚህ ሀቅ በመነሳት የዛሬው አገዛዝና ገብረአበሮቹ ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ጫንቃ ላይ እንዲወገዱ የበኩሉን የትግል አስተዋጽኦ እያደረገ፣ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጪ ተደራጅተውም ሆነ ሳይደራጁ ፣ ለዲሞክራሲ መታፈን፣ ለሰላም መደፍረስ፣ ለብሔራዊ ነጻነት መገፈፍ የሚቆረቆሩ ኢትዮጵያውያን ድርጅቶችና ግለሰቦች ኃይላቸውን ከርዕዮተ ዓለም ባሻገር ሰብስበውና አስተባብረው የጋራ ጠላታቸውን በተባበረ ክንድ እንዲደመስሱ የሀገር ፍቅር ስሜት የተሞላበትን ጥሪውን ያስተላልፋል ።ከጎናቸውም ቆሞ ይታገላል ።

## የብሔራዊ ነጻነት ጥያቄ

ከውስጥ ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ባልሰፈነበት ሀገር፣ ጥቂት የገዢ መደቦች በጥቅም ተሳስረው ሕዝብን በጠበንጃ አፈሙዝ አፍነው በሚገዙበት ሀገር ብሔራዊ ነጻነት ይከበራል ማለቱ ዘበት ነው ። እንደነዚህ ዓይነት የገዢ መደቦች በሕዝብ ላይ እምነት ስለማይኖራቸው ሁል ጊዜ እጃቸውን ወደ ውጪ ዘርግተው፣ የውጪ ኃይሎችን በማስገባት አንዱን ሀገር ተቀጥያ እንደሚያደርጉ በታሪክ ተደጋግሞ የታየ ሀቅ ነው ። በዚህም፣ ማንኛውም ለብሔራዊ ነጻነቱ ተቆርቋሪ የሆነን ኃይል በሙሉ አጥፍተው የሥልጣን ዘመናቸውን ለማርዘም ከፍተኛ መፍጨርጨር እንደሚያደርጉ የታወቀ ነው ።

ዛሬ በሀገራችን ላይ የተንሰራፋው አምባገነናዊ የወታደር አገዛዝ፣ ሕዝባችንን ለጦርነት ከመማገዱ አልፎ የውጪ ኃይሎች ወደሀገራችን በማስገባት ሀገራችንን በዓለም ሸንጎ ፊት እንዳዋረዳትና፣ ከውስጥ ደግሞ ሕዝባችንን በእነዚህ ዘረኞች ፊት ዝቅተኛ እንዳደረገ የታወቀ ሀቅ ነው ። እነዚህ ዘረኞች በሚገቡበት ሱቅና ሆቴል ቤቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳይደርስ ሆኖ ባሀገሩ ባይተዋር እንዲሆን ተደርጓል ። ይህ ለማንኛውም ሀቀኛ ኢትዮጵያዊ ጭንቀትን የሚነክን ትልቅ ውርደት ለመሆኑ ገልጽ ነው ። ይህንን እንዲያው አነሳነው እንጂ፣ የሶቭየት ኅብረትና ኅብረ አበሮቿ ይህንን የዘረኝነትና የጌትነት በላይነት የተቀዳጁት ሀገራችንን በመጀመሪያ በጦር መሣሪያ ዕርዳታ ስም ቀስ በቀስ በዕዳ ከጠፈሯት በኋላና በአማካሪነት ስም የሚሊተሪውን ተቋም በቁጥጥራቸው ስር እያደረጉ ከመጡ ወዲህ ነው ። እነዚህ የውጪ ኃይሎች እርስ በእርሳቸው የሥራ ክፍፍል በማድረግ፣ አንደኛው በሚሊታሪ ውስጥ ሌላው በኢኮኖሚና በፀጥታ ውስጥ የበላይነትን በመቀዳጀት፣ በአንድ በኩል በየክፍሉ የሚሠሩ ሀገር ወዳዶችን የበታቾቻቸው ሲያደርጉና ሲያዙ፣ በሌላ በኩል የተቀዳጁትን የበላይነት ተገን በማድረግ ሀብታችንን በገፍ እየበዘበዙና ሀገራችንን እያራቆቱ ነው ።



ሌላው ቢቀር እንኳ፣ ዛሬ ሕዝባችን በከፍተኛ ረሀብ በመሰቃየበት ወቅት፣ በሀገሪቱ ውስጥ የሚመረቱት የእርሻ ውጤቶች ወደእነዚህ የምሥራቅ አውሮፓ ሀገሮች በገፍ እየተጋዙ ነው ። ይህም የሚያሳየው እነዚህ ሀገሮች ምን ያህል የበላይነትን የተቀዳጁ መሆናቸውን የሚያመለክቱ ናቸው ። ይህንን የበላይነት ሞኖፖል እንደያዙ ለመቆየት፣ ሶቭየት ኅብረትና ኅብረአበሮቿ፣ በአንድ በኩል ለወታደሩ መንግሥት በገፍ መሣሪያ በማቀበል ሀገሪቱ ወደሌላ የእርስ በእርስ ጦርነት በየጊዜው እንድትማገድ ሲያደርጉ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የወታደሩ መንግሥት የጎረቤት ሀገሮችን እንዲተናኮል በማድረግ በአካባቢ ሀገሮች ሰላም እንዲደፈርስና ሕዝባችንን ለሌላ አሰቃቂ ጦርነት እየጋበዙት ነው ። እንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታም በአካባቢው ሀገሮች የሁለቱን ኃያላን መንግሥታት አሽቀዳድሞ ከማባባሱም ሌላ፣ የሶቭየት ኅብረትና የኅብረአበሮቿ በሀገራችን መኖር እየተራዘመ እንደሚሄድ ገልጽ ነው ።

ከዚህ ሀቅ በመነሳት፣ እነዚህ የውጪ ኃይሎች ከሀገራችን እስካልወጡ ድረስና ኢትዮጵያም ብሔራዊ ነጻነቷን እስካልተጎናጸፈች ድረስ በሀገራችን ሰላምና ዲሞክራሲ፣ እንዲሁም ብልጽግና ለመስፈን ስለማይችሉ፣ በሬው የኢትዮጵያ ሕዝብ በወታደሩ መንግሥትና በእነዚህ የብሔራዊ ነጻነታችን ጠንቅ በሆኑ የውጪ ኃይሎች ላይ የጋራ ክንዱን እንዲያነሳ ይህ ንቅናቄ ጥሪውን ያስተላልፋል ።

## ኢ ሠ ፖ አ ኮ

ማኅበራችን፣ ስለዚህ በኢትዮጵያ ሠርቶ አደሮች ስም ስለተቋቋመው የጥቂት ምርጥ መኳንንቶች፣ የሲቪልና የሚሊተሪ ቢሮክራሲው እንዲሁም የለየላቸው አድር ባዮች ጕርና የሆነውን ኮሚሽን፣ ፀረ–ሕዝብ ፣ ትምክህተኝነት፣ ፀረ–ዲሞክራሲና በፍጹም የኢትዮጵያን ወዝ አደሮች የማይወክል መሆኑን በማሳየት ባለፉት ዓመታት በተከታታይ አቋም የወሰደ ለመሆኑ ይታወቃል ። ይህ ኮሚሽን ከተፀነሰ ጀምሮ ያረጋገጠው ነገር ቢኖር፣ የየካቲት አብዮት የወለዳቸውን ልዩ ልዩ የፖለቲካና ሕዝባዊ ድርጅቶች በሕገ በመሸርና አንዳንዶቹንም በጉልበት በመደምሰስና የራሱ ተቀጥያ በማድረግ የወታደሩን መንግሥት የፈላጭ ቆራጭነት ለማረጋገጥ እንደሆነ እስካሁን የተጓዘው ጉዞ በቂ ማስረጃ ነው ።

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር፣ ከዚህ በፊት እንዳደረገው ሁሉ፣ ይህ ፀረ–ሕዝብና ትምክህተኛ ኮሚሽን በፍጹም የኢትዮጵያን ወዝ አደሮችና ገበሬዎች እንዲሁም የነቁ ተራማጆችን የማይወክል መሆኑን በዓለም ፊት እያጋለጠው፣ ለሀቀኛ የወዝ አደር ፓርቲ መመሥረት ለሚታገሉ ተራማጅ ድርጅቶች የትግል አንድነቱን እንደገና ያረጋግጣል ።

## ስለብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት

በመሠረቱ በአንድ ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር በአለት አገር ውስጥ፣ የአገሬው ዜጋ እናት አገሩን ከውጪ ጠላት ለመከላከልና ዳር ድንበሩን ለመጠበቅ ማንኛውም አካለ ሙሉ የሆነ ዜጋ ብሔራዊ የውትድርና አገልግሎት ለመስጠት መዘጋጀቱ በማንኛውም አገር ወዳድ ታጋይ የሚደገፍ በጎ ተግባር ነው ብሎ ማኅበራችን ያምናል ። በኢትዮጵያ ግን ታሪኩ ሌላ ነው ። የወታደሩ ፈላጭ ቆራጭ መንግሥት፣ በአንድ በኩል ሥልጣኑን ለማደላደል ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎችን እያፈነና



እየመታ፣ በሌላ በኩል " የእናት አገርን ዳር ድንበር የግዛት አንድነት " ለመጠበቅና " ተገንጣዮችን " ለመደምሰስ በሚል አወናባጅና አድኃሪ መፈክር ሕዝቦችን እርስ በእርስ እያጋጨና ሀገራቸውን ጥለው እንዲሰደዱ እያደረገ፣ እንደዚህ ዓይነቱ ዘመቻ በምንም ዓይነት በሀገር ወዳዶችና በዲሞክራቲክ ኃይሎች አይደገፍም ።

አገራችን በአፍሪካ እጅግ የቆረቆዘችና የደሆች ደሃ የሆነች ሀገር መሆኗ እየታወቀ፣ ካለው በብዙ መቶ ሺህ ከሚገመተው ቋሚ ወታደርና ሚሊሺያ አልፎ ወጣቱን ትውልድ በአሁኑ ወቅት ለጦርነት እንዲዘጋጁ ማድረግ፣ በአንድ በኩል ይህንን ወጣት ትውልድ የእሳት እራት ሲያደርገው፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሀገሪቱን ሀብትና የወደፊቱ ሠራተኛ ሕዝብጠቃሚ ባልሆነ ቦታ ላይ እንዲውሉ ተደርገው፣ ሀገሪቱ ወደ ባሰ ድህነት እንደምትገፈተር ገልጽ ነው ። ከዚህ በተረፈ፣ ይህ ዘመቻ የሀገሪቱን ሕዝብ ሚሊታሪዝም ከማድረግ አልፎ በሕዝቦች መሀከል የባሰ መቃቃርን፣ እርስ በእርስ መጠላላትን ወደሚያስከትል ጦርነት ለመከተት የሚደረግ አደገኛ ዘመቻ እንደሆነ ማኅበራችን ይገምታል ። ማኅበራችን፣ ይህን በሰፊው ሕዝብ ያልተደገፈና የጥቂት አድኃሪ ኃይሎችን ዕድሜ ለማራዘም የታቀደውን ዘመቻ አጥብቆ እየተቃወመ፣ ወጣቱ ትውልድ አፈሙዙን በዚህ ፀረ–ሕዝብ መንግሥት ላይ እንዲያነሳ ጥሪውን ያቀርብለታል ።

## ብሔር/ብሔረሰቦችን በሚመለከተው በኩል

አኢተማ በ1971 ዓ.ም በ11ኛው ጠ/ጉባዔ ላይ ለብዙ ጊዜ በኢትዮጵያ ተራማጆች ዘንድ ሲያከራክር በነበረው የብሔር/ብሔረሰቦች ጥያቄ ላይ የማያወላውል ትክክለኛ አቋም ከወሰደ ወዲህ፣ በየዓመቱ በሚደረጉት ጠ/ጉባዔዎች ላይ ለዚህ አቋሙ ታማኝ ሆኖ፣ አሁንም ለማይገረሰሰው የብሔረ/ብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እንዲከበር ትግሉን እንደቀጠለ ነው ። ዛሬ፣ የታሪክ ክስተት ሆኖ

በሀገሪቱ ውስጥ ከመደብ ትግል ይልቅ የብሔር/ብሔረሰቦች ትግል እየጐላ መምጣቱና ጭቁን ብሔር/ብሔረሰቦችም ትግላቸውን ከምንጊዜውም የበለጠ በማፋፋማቸው፣ ይህ ጥያቄ ከቲዎሪ ደረጃ አልፎ ወደ ተጨባጭ ድርጊት መሸጋገር ያለበት መሆኑን በመረዳት፣ ጉባዔው ሰፊ ውይይት አካሂዷል ። ለዚህም፣ ማኅበራችን ተገባራዊ ነው የሚላቸውን የጊዜውን ተጨባጭ ሁኔታ በመገንዘብ፤ በአንድ በኩል ልዩ ልዩ የብሔር/ብሔረሰብ እንቅስቃሴዎችና ሌሎች የአገር አቀፍ ተራማጅ ድርጅቶች ወደ አንድ የተቀነባበረ ትግል እንዲያመሩ የበኩሉን ማንኛውንም ዓይነት ድጋፍ ለመስጠት መዘጋጀት ሲኖርበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በብሔር/ብሔረሰብ የተማሪ እንቅስቃሴዎች ጋር አብሮ በመሥራትና በበኩሉም ብቦታቸውንና አሳማቸውን በማስጠት የትግሉ አንደኛው ክፍል መሆኑን በመረዳት፣ በዚህ ላይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እንደሚሠራበት በጉዳዩ ላይ ተነጋግሯል ። ከዚህ በተጨማሪ ጉባዔው በዚህ ጥያቄ ላይ ከአሁኑ የበለጠ ሰፊ ጥናት እንዲያካሂድ ወስኗል ።

በዚህ ወቅት ይህ ጉባዔ፣ ከዚህ በፊት ድጋፍ ለሰጣቸው የብሔር/ብሔረሰብ እንቅስቃሴዎች ማለትም፣ ለኢፒኤልኤፍ /EPLF /፣ ቲፒኤልኤፍ/TPLF /፣ ኦኤልኤፍ /OLF / ፣ ሲዓማ፣ አብዒን እንዲሁም ለሱማሌ ብሔረሰብ ታጋዮች የሰጠውን ድጋፍ አያደሰ፣ ትግላቸውን አስተባብረው በጋራ እንዲታገሉ አብዮታዊ ጥሪ ያቀርብላቸዋል ።

## ስለ ፖለቲካ አስረኞችና ስደተኞች

የ1977 ጽልመት ኢትዮጵያን በፖለቲካ አስረኞች ቁጥር ከአፍሪካ የመጀመሪያ አገር እንዳደረጋት ማኅበራችን ደጋግሞ ያስታወሰው ጉዳይ ነው ። ከ30 000 በላይ የሚሆኑ አገር ወዳዶችና ዴሞክራቶች አሁንም በወታደሩ መንግሥት እስር ቤት ይማቅቃሉ ። የደረሱበት ያልታወቀ ተራማጆች ቁጥር ምን ያህል እንደሆነ ለጊዜው



አጠቃላይ ስታትስቲክስ ባይወጣም፣ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ይህም አልበቃ ብሎአቸው፣ በያዝነው ዓመት ብቻ ብዙ የጭቁን ብሔር/ብሔረሰብ ታጋዮችና ደጋፊዎች እየተለቀሙ ወደ እስር ቤት እንደተወረወሩ ይታወቃል ።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ዴሞክራት መስሎ ለመቅረብና የወጣውን ዕርዳታ ለመቀራመት ሲል ባለፈው መስከረም ወር 1975 በጣት የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች ቢፈቱም፣ አሁንም በብዙ ሺህ ታጋዮች እስር ቤት እንደሚሰቃዩና ከተፈቱት ይልቅ በየጊዜው የሚታሰሩት ስለሚበልጡ፣ የደርግ ፀረ-ዴሞክራቲክነት በፍጹም እንዳልተቀየረና በተራማጆች ላይ የሚያደርገውን የአፈናና የእስራ ዘመቻም ጋብ እንዳላደረገው ይህ ጉባዔ በጥብቅ ያምናል ። ከዚህ በመነሳት ጉባዔችን ከዚህ በፊት ደጋግሞ እንዳደረገው ሁሉ ድርጊቱን አጥብቆ አያወገዘ የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ የሚያደርገውን ትግሉ ይቀጥላል ።

ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ የስደተኞች ጥያቄ ነው ። ዛሬ በዓለም ካሉት ስደተኞች የመጀመሪያውን ደረጃ የያዙት ኢትዮጵያውያን ናቸው ። በሌላ ወገን ደግሞ የጐረቤት አገሮች የኢትዮጵያን ስደተኞች ማስተናገድ ስለአቃታቸው ለተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽን አቤት ማለት ከጀመሩ ጊዜው በንብቷል ። በተለይም በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያና በጅቡቲ መካከል በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን አስተባባሪነት የተደረገው ስደተኞችን ወደ አገራቸው የመመለሱ ጉዳይ ነገሩን የበለጠ አሳሳቢ አድርጎታል ። በውሉም መሠረት ብዙዎቹ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ ከምፕ ውስጥ ሲገቡ፣ ሌሎች ደግሞ እስር ቤት ተልከዋል ። የሚጠብቀውን ፍዳ አልቀበል ያለው ደግሞ ከባቡር እየተወረወረ ሕይወቱን አጥቷል ። ማኅበራችን ይህን የስደተኞችን በግድ ወደ ሀገር ቤት አስገድዶ የመመለስ ጉዳይ በጥብቅ አያወገዘ፣ ተቃውሞውን ለሰብአዊ መብት መገርሰስ ለሚቆረቆሩ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሁኔታውን እየተከታተለ እንደሚያስታውቅና ተቃውሞአቸውን እንዲያሰሙ ጥሪ እንደሚያስተላልፍላቸው በዚህ በጉባዔ ላይ በአንድ ድምጽ ወስኗል ።

## የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ

ዛሬ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ሁኔታ ጠለቅ ብለን ስንመረምረው፣ ደቀና አያሌ መመስቃቀሎች ደርሰውበት ይታያል ። ለሁኔታው መባባስና መመሰቃቀል ዋናው ተጠያቂ በሥልጣን ላይ ያለው አምባገነኑ የወታደር መንግሥትና ገብረ አበሮቹ ሲሆኑ፣ በዚህ መንግሥት ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ የወጡት "የአረንጓዴ የምርት ዘመቻና" "ሌሎች" የኢኮኖሚ ዕቅዶችና መመሪያዎች" ሀገሪቱ ለዘፈቀችበት ችግርና ሕዝቡ ለደረሰበት የዕለት ተዕለት ችግር መፍትሔ ሊሰጡ ባይችሉ ቀርተዋል ።

የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ጤናማ በሆነ መልክ አድጎ የሕዝቡን ፍላጎት ሊያሟላ የሚችለው በየጊዜው "የኢኮኖሚ ዕቅድ" መውጣቱ በቻ ባይሆን፣ ይህ በየጊዜው የሚወጣው ዕቅድ በሥራ ላይ ሊውል የሚችለው፣ እንደኛ ዲሞክራሲና በሳም ሰፍነው ሕዝቡ በቀጥታ በኢኮኖሚ ግንባታ ውስጥ ተሳትፎ ያደረገ እንደሆነ፣ ሁለተኛ የሚወጣው ዕቅድ በተጨባጭ የሀገሪቱን ሁኔታ የሚያንጸባርቅና ሀገሪቱን በተመጣጠነ መልክ ሊያሳድግና በተግባር ሊተረጎም የሚችል እንደሆነ ብቻ ነው ። በተለይም በአሁኑ በተወሳሰበ የዓለም ሁኔታ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የመጨረሻ ደሃ ሀገሮች ያለባቸውን የኢኮኖሚ ችግር በጥቂት ቴክኖክራቶችና ማኔጀሮች ሊወጡት አይችሉም ። የግዴታ የሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎና ሰላም በሀገሪቱ መስፈን መሠረታዊና ለኢኮኖሚው ችግር መፈታት እንደስትንፋስ የሚያስፈልጉት ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው ።

የዛሬውን አገዛዝ የተመለከትን እንደሆነ ደግሞ፣ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች የማያሟላ ብቻ ባይሆን አያበላሽ የመጣና ለዛሬው ምስቅልቅል ሁኔታ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ነው ። የወታደሩ መንግሥት ወደአምባገነንነት ከተለወጠ ከስድስት ዓመታት በፊት ጀምሮ የሕዝቡን ዲሞክራሲያዊ መብት አፍኖ በአራቱም ማዕዘን በጭቁን ብሔር /ብሔረሰቦች ላይ ጦርነት እያካሄደ ለመሆኑ የታወቀ ነገር ነው ። አንድ መንግሥት እንደዚህ ዓይነት ጦርነት ሲያካሂድ ደግሞ



የግዴታ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚመረተውን የእርሻም ሆነ የኢንዱስትሪ ምርት አብዛኛውን ለዚህ ጦርነት ማዋል አለበት ። እንደዚህም ብዙ ሰው ለጦርነት ማሰማራት አለበት ። በመሆኑም፣ የኢኮኖሚው ሰርፕለስ ጠቃሚ /ፕሮዳክቲቭ/ በሆነ መስክ ላይ ሊሰማራ ስለአልቻለና ስለማይችል፣ ዛሬ ከእርሻው መስክ አንስቶ የኢንዱስትሪውን መስክ አቋርጦ እስከ አገልግሎት ድረስ፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ደቀና ተዘብቶ ይገኛል ።

የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ችግር በሚገባ ለመረዳት የኢኮኖሚውን መዋቅር /ስትራክቸር/፣ ማለትም፣ የኢንዱስትሪውን፣ የእርሻውንና የአገልግሎቱን ሁኔታ ጠለቅ ብሎ መመርመር ያስፈልጋል ።

እንደሚታወቀው፣ በሀገራችን በ50ኛውና በ60ኛው ዓመታት በኢምፔሪያሊዝም ገፊት የተቋቋሙት ኢንዱስትሪዎች በራሳቸው ውስጠ ኃይል ማነስ / / Dynamic / ሳይሆን፣ ኢንዱስትሪዎችን በሚቀጣጠሩትና ኢንዱስትሪያችም በቀጥታ ከውጪ ጥገኛ በመሆናቸው ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ መዳበር እስከዚህም አስተዋጽኦ ሳያበረክቱ ቀሩ ። ከዚህም ሌላ የውጭ ሀገር ሰዎች ቀጥተኛ የሆነ ወሳኝ ሚና በኢንዱስትሪዎቹ ላይ በመጎናጸፋቸው ሰፊው የኢትዮጵያ ወዝአደርና አርሶ አደር የምርቶቹ ተጠቃሚ ለመሆን ባለመቻሉ የኢንዱስትሪዎቹ የማደግና የማስፋፋት ዕድል በጣም ዝቅተኛ ሆኖ እንዲቀር ተገደደ። በእነዚህም ኢንዱስትሪዎች ተቀጥሮ የሚሠራው ወዝ አደር የቀን ደመወዙ ከአንድ እስከ ሁለት ብር ብቻ በመሆኑ፣ እራሱ ያመረታቸውን የኢንዱስትሪ ውጤቶች ገዝቶ ፍላጎቱን ሊያሟላ አልቻለም ። የኢንዱስትሪዎቹም ተጠቃሚ በጣም ጥቂት የኅብረተሰብ ክፍል ብቻ ሆነ ።

ከየካቲት አብዮት በኋላና እስከ አሁን ድረስ ያለውን ሁኔታም ስንመለከት፣ ኢንዱስትሪዎቹ ከመወረሳቸው በስተቀር፣ በአሠራር፣ በወዝአደሩ ደሞዝ በጣም ዝቅተኛ መሆንና አሁንም እንደ ቀድሞው የምርቶቹ ተጠቃሚ ባለመሆን፣ በኢንዱስትሪዎቹ የውጭ ጥገኛ መሆን / በጥሬጥሬ፣ በናሃው፣ በመለዋወጫ ዕቃ/

ሁኔታው በፍጹም እንዳልተለወጠ እንረዳለን ። " በአንቀርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ ፤ እነዚህ ኢንዱስትሪዎችም በደርግ ፀረ ዲሞክራትነትና በወዝ አደሩ የመፍጠር ችሎታ መታፈን ፤ በቀለጠፈ የአሠራር ጉድለት ፤ በኢንዱስትሪዎች ማርጀትና በዕቃ መለዋወጫ እጥረት ... ወዘተ ከአስር ዓመት በፊት ከነበረው የማምረት ችሎታ / Capacity /በሚስተካከል ሁኔታ እንኳን አምርተው የሰፊውን ሕዝብ ፍላጎት ለማሟላት አልቻሉም ። በመሆኑም ዛሬ በሀገሪቱ ውስጥ ሰፋ ያለ የኢንዱስትሪ ምርት እጥረት አለ ። የሚገኙትም ዋጋቸው በጣም ውድ ከመሆኑ የተነሳ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ገዝቶ ሊጠቀምባቸውና ፍላጎቱን ሊያረካ አልቻለም ። በመሆኑም ፤ ዛሬ በዕቃዎች እጥረት ብቻ ሳይሆን፤ በዋጋቸውም መናር ና በሰፊው ሕዝብ መግዛት አለመቻል፤ ሰፊው ሕዝብ በድኅነት እየማቀቀ መሆኑ የታወቀ ነገር ነው ። በዕቃዎችም እጥረት የተነሳ፤ በሀገሪቱ ውስጥ የጥቁር ገበያ ቀጥ በአጣ መልኩ ተስፋፍቶ በኢኮኖሚው ላይ አሉታዊ ውጤት እንደጣለ ይታወቃል ። ሊቀመንበሩ አራቱ፤በታኅሳስ ወር 1975 ዓ.ም በኢሠፖአኮ 2ኛ ጉባዔ ላይ በአደረገው ንግግር በጥቁር ገበያ መስፋፋት የተነሳ ወደ ውጪ የሚወጡት የሀገር ቤት የማዕድንና ሌሎች የጥሬጥሬ ሀብቶች ፤ እንዲሁም ከወጪ ወደ ሀገር ቤት የሚገቡ የኢንዱስትሪ ውጤቶች በ1972 ዓ.ም ወደ 102 ሚሊዮን ብር እንደደረሱ አስታውቋል ። በአሁኑ ወቅትም ሁኔታው ከዚህ የባሰ መሆኑ ግልጽ ነው ። ከዚህ በተረፈ፤ እነዚህ ከ30 ዓመታት በፊት የተቋቋሙት ኢንዱስትሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ በከተማዎች መስፋፋትና ማደግ ከገጠር ወደ ከተማ እየፈለሰ ለመጣው ሥራ ፈላጊ ሕዝብ የሥራ ዕድል ለመስጠትና ገቢ አግኝቶ የምርቶቹ ተጠቃሚ ለማድረግ ስላልነበር፤ በትላልቅ ከተሞች በተለይም በአዲስ አበባ የተከማቸው ሥራ ፈላጊ በእነዚህ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የመቀጠር መብት አላገኘም ። በመሆኑም፤ ይህ ሥራ አጥ ሕዝብ ወደሌሎች መስኮች ማለትም ወደ ሌብነት፤ ማጅራት መቺነት፤ ቤተኛ አዳሪነት፤ ሊስትሮነት፤ ውኃ ቀጂነት በመሠማራት ጠቃሚ / ፕሮዳክቲቭ / ሳይሆን ቀረ ።



ዛሬም ዘጠኝ ዓመታት በኋላ ይህ ሁኔታ በፍጹም አልተቀየረም ። እንዲያውም የሥራ አጡ ቁጥር ከመብዛቱ የተነሳ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ማጅራት መቺነት፤ ሌብነት ፤ ቤተኛ አዳሪነት ፤ ለማኝነት ... ወዘተ ከምን ጊዜውም የበለጠ ተስፋፍተው ይገኛሉ ። እንግዲህ ይህ መንግሥት ይህንን ሁኔታ በማጤን በድብቅ ሥራ አጥነትና በሥራ አጥነት ለሚሰቃየው ሕዝብ አዳዲስ የሥራ መስኮች ለመክፈት የማይችል ብቻ ሳይሆን የማይፈልግም መሆኑን በተግባር አስመስክሯል ።

የእርሻ መስኩንም የተመለከትን እንደሆነ፤ ችግሩ የባሰ እንጂ ከላይ ከተጠቀሰው ሁኔታ የተሻለ አይደለም ። ሁኔታውን ለመረዳት የመንግሥት እርሻዎችና በግል የሚታረሱትን ነጣጥሎ መመልከት ያስፈልጋል ።

እንደእውነቱ ከሆነ በየካቲት ወር 1975 ዓ.ም የታወጀው የመሬት አዋጅ በከፊል እንኳን በሥራ ላይ ቢውል ኖሮ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በድጋሚ በእንደዚህ ዓይነት አሰቃቂ ረኃብ ባልተጋለጠ ነበር ። በአንድ ሀገር ውስጥ መሬትን የሰፊው ሕዝብ ሀብት እንዲሆን ማድረጉ ብቻ በቂ አይደለም ። ለመሬት አዋጁ በሥራ ላይ መዋል የዲሞክራሲ ጥያቄ መፈታት እንደእስትንፋስ የሚያስፈልገው ነው ። የዲሞክራሲን ጥያቄ ለመፈታት ደግሞ በሕዝብ የተደገፈ ህቀኛ የሆነ ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ያስፈልጋል ። ከዚህ በተረፈ ብቁ የሆኑና ለሰፊው ሕዝብ ለማገልገል የተዘጋጁ ካድሬዎች ማሰናዳት ያስፈልጋል ።ማለትም በአወቅሁኝባይነት በሰፊው ገበሬ ላይ የሚደነፉ ካድሬዎች ሳይሆኑ፤ ከሱ ለመማር እሱን መልሰው ለማስተማር፤ ከእሱ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው አዲሲቱን ኢትዮጵያ ለመመስረት የሚችሉ ሰዎችን ማሰማራት ያስፈልጋል ማለት ነው ። ከዚህ በላይ፤ የእርሻ ምርትን ከፍ ለማድረግ የግዴታ ቢያንስ ከድሮው የተሻሉ የምርት መሣሪያዎችን ለአራሹ ሕዝብ ሊቀርብ የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል ። ይህንን ደግሞ በአገሪቱ ውስጥ ያሉት ቀላል የብረታብረት ፋብሪካዎች ሊያሟሉ የሚችሉበትን ዘዴ ጥናት ማካሄድ አስፈላጊ ነው ።ለዚህ ደግሞ የሃሳብን፤የመመራመርን ችግር ለመፍታት አሁንም ዘር ዘር የዲሞክራሲን ጥያቄ መፍታት ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል ።ዲሞክራሲያዊ መብቶች በታፈኑበት ሀገር ሐሳብን ለማስፋፋትና ለችግሮች

መፍትሔ ለመስጠት በፍጹም ስለማይቻል ነው ::

የዛሬው አገዛዝ ግን ይህንን ሊያደርግና ለማድረግ አልቻለም :: ይልቁንስ የታየው፣ የሰፊውን ሕዝብ መብት በጧማው ጨፍልቆ የሥልጣን ዘመኑን ለማርዘም ነው :: በመሆኑም በአገዛዙ ፀረ-ዲሞክራሲነት፣ አብረው በተባበሩት ጥቂት ደንጌያችና በቢሮክራሲው ግድየለሽነትና አድኃሪነት፣ ገበሬው የምርት መሣሪያዎችን አሻሽሉና የተሻሉ የምርት መሣሪያዎችን ገዝቶ በመጠቀም በነጻ አርሶ በቀላሉ የምርቶቹ ተጠቃሚ አልሆነም ::በሌላ በኩል ያመረተውን ምርት ገበያ ላይ አውጥቶ ሸጦ በአገኘው ገንዘብ እንደፈለገው በተመጣጣኝ ዋጋ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ገዝቶ ሊጠቀም አልቻለም :: ከዚህ በተረፈ፣ በጉልበት የተቋቋሙት የኅብረት አርሻዎችም እንደተፈለገውና እንደታቀደው የአርሻ ምርትን ከፍ ለማድረግ አልቻሉም :: ከሕዝብ ፍላጎት ውጪ በጉልበት የሚደነገግ ማንኛውም ተግባር የመጨረሻ መጨረሻ ውጤቱ የማያምር መሆኑን ይህ ድርጊት በቀላሉ አስመስክሯል :: በመሆኑም፣ ዛሬ በከተሞች አያሌ የጤፍ፣ የበቆሎ፣ የገብስና የስንዴ፣ የጥራጥሬ / አተር፣ ሽምብራ፣ ባቄላ ... / እጥረት ሰፍኖ ይገኛል :: ያሉትም በጣም ውድ ከመሆናቸው የተነሳ ሰፊው የከተማ ሕዝብ በቀላሉ ገዝቶ ሊመገብ አልቻለም :: እንደእውነቱ ከሆነ፣ ዛሬ ሳለው የምግብ እጥረትና ረሐብ፣ ሊቀመንበሩ ለመራቀቅ እንደሚለው " ችግራችን የሳይንስና የቴክኖሎጂ ባይሆን " ፣ ዋናው ችግራችን ዛሬ በሥልጣን ላይ ያለው ወታደራዊ አገዛዝ፣ ቢሮክራሲውና እንደዚሁም የውጪ ኃይሎች የፈጠሩት ፀረ-ዲሞክራቲክ አገዛዝና ምስቅልቅል ሁኔታ ነው :: ነገር ግን፣ ሊቀመንበሩ በዚህ አባባሉ ያልተረዳው፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ማደግና መስፋፋት ከዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈንና የነጻ አስተሳሰብ መበልፀግ ጋር በጥብቅ የተያያዘ መሆኑን ነው :: ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሌሉበት፣ የሰፊው ሕዝብ አስተሳሰብ በታፈነበት፣ የውጪ ኃይሎች በነገሡበት ሀገር ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሊያድጉ አይችሉም ::

በተጨማሪ ፣ ለአርሻ ምርት መቀነስና ለእህል መጥፋት ሌላው ምክንያት ብዙ ወጣት ገበሬዎች ወደጦር ሜዳ በመዝመታቸውና አንዳንዱ የአርሻ መስኮች ወደ



ጦር አውድማ በመለወጣቸውም ነው :: ከዚህ ጋር ተያየዘና ከላይ ቀደም ብለን በጠቀስናቸው ምክንያቶችና ድርቅ በመግባቱ፣ ዛሬ በሰሜን ኢትዮጵያ፣ በጎንደር፣ በወሎ፣ በትግሬ ፣ በኤርትራ ትልቅ ረሃብ ገብቶ ሕዝባችንን እየጨረሰ ነው :: የተራበው ሕዝብ ቁጥር ከስድስት ሚሊዮን እንደሚበልጥ ይገመታል ::

የመንግሥት አርሻዎችንም የተመለከትን እንደሆነ፣ ሊቀመንበሩ በታኅሣሥ ወር 1975 የኢሠፓአኮ 2ኛ ጉባዔ ላይ ባደረገው ንግግር አሰባቢ ቦታ ላይ እንደሚገኙ በማመን ተናግሯል :: በዚህ መስክ የሚታየው ችግር ያሉትን የምርት መሳሪያዎች በስነ ስርዓት አለመያዝና የተበላሹትንም እያደሱ ለተግባር ማዋል አለመቻሉ ነው :: ከዚህም የተነሳና በጠቅላላው ባለው ዝርክርክ አሠራር የመንግሥት አርሻዎች ሊሰጡ የሚገባቸውን ውጤት ሊያሟሉ አልቻሉም :: ይህም ከግድየለሽነትና ካለው ሥርዓት ጋር የተያያዘ ነው :: ዲሞክራሲ በጠፋበት ሀገር፣ ለሥልጣን፣ ለጥቅም ብቻ በሚቋምጥበት ሀገር ግድየለሽነት እንደሚስፋፋ የታወቀ ነው ::

የአገልግሎትንም ሁኔታ የተመለከትን እንደሆን በጣም የተዝረከረከ ሆኖ እናገኘዋለን :: ይህ መስክ በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ በአጭር ጊዜ ውስጥ አንዱ ላይ አጠናቅሮ ለማቅረብ ያስቸግራል :: ማለት የሚቻለው ግን፣ ከየካቲት በፊት ያሉት ሁኔታዎች በፍጹም እንዳልተለወጡና እንዲያውም ዛሬ የባሰውኑ ተዘበራርቀውና ተበላሽተው እንደሚገኙ ነው :: ካፒታሊዝም ወደ ሀገራችን ሲመጣ ብዙ ገንዘብ ያላቸውን ወደዚህ መስክ እንዲሰማሩ አስገደዳቸው :: ይህውም፣ ሆቴል ቤት መክፈት፣ ቡና ነጋዴ መሆን፣ ጠጅ ቤት፣ ሻይ ቤት ... ወዘተ ፣ እነዚህን የመሳሰሉት መስፋፋት የሀገሪቱን በዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም ሥር ጥገኛ እየሆነች መምጣትና ኢኮኖሚዋም እየቀረቀዘ እንዲሄድ መደረጉን ያመለክታል :: በመሆኑም የሀገሪቱ ሀብት ጠቃሚ /ፕሮዳክቲቭ/ በሆነ መስክ ላይ ሊውል አልቻለም :: በተቃራኒው ግን የሀገሪቱ ካፒታል የውጪ ካፒታሊስቶችን ሸቀጥ ለማራገፊያ እንዲውል በመደረጉ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ መዳበር ትርጉም ያለው ሚና ሳይጫወት ቀረ :: ዛሬ ደግሞ ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ የተስፋፋው ነገር ቢኖር ይኸው ከላይ የተጠቀሰው የንግድ መስክ ነው ::ይህም ሁኔታ የሚያመለክተው ፣

የሀገሪቱን ኢኮኖሚ መዳሸቅና መዘበራረቅ እንጂ የአንዱን ሀገር ጤናማ ሁኔታ የሚያመለክት አይደለም ። በዚህም ምክንያት ካፒታል ወደአልሆነ አቅጣጫ መስመሩን እንዲስት እየተደረገ ነው ። ያለው መንግሥት ደግሞ ይህንን ሁሉ አጤና በተገባር ሊመነዝር የሚችል . . የኢኮኖሚ ዕቅዱ ለማውጣት የማይችል በመሆኑ ይህ ሁኔታ ከቀጠለ የሀገሪቱ ችግር እየሰፋና ጥልቀትን እያገኘ እንደሚሄድ ግልጽ ነው ።

የወጪውን የንግድ ሚዛንም የተመለከትን እንደሆነ፣ ከ1975 ዓ.ም ጀምሮ ኔጋቲቭ ሲሆን፣ ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ ይበልጥ እየተዛባና ከውጪ የምናገኘው ምንዛሬ በጣም እየቀነሰ መጥቷል ። የ1981–82 የንግድ ሚዛን ስንመለከት – 826.3 ሲሆን፣ በ1982–83 ባለው ጊዜ ውስጥ የንግድ ሚዛኑ ወደ – 896.6 አሽቆልቁሏል ። ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ስንነሳ ይህ ሁኔታ ወደፊት እንደሚቀጥል ለመረዳት እንችላለን ። ሀገሪቱ አሁንም እንደወትሮው ለውጪ ገበያ የምታቀርበውን ምርት ልትለዋወጥና ሌሎች አዳዲስ ደንበኞች ልታፈራ አልቻለችም ። የተደረገው የውጪ ንግድ ግንኙነት ለውጥ ከምሥራቅ አውሮፖ ሀገሮች ጋር ያለው የንግድ ልውወጥ ነው ። ለምሳሌ ከሶቭየት ኅብረት ጋር የሚደረገው የንግድ ልውውጥ ከጠቅላላው የውጭ ንግድ 16 ከመቶው ይዟል ። ከእነዚህ ሀገሮችም ደግሞ የሚመጣው አብዛኛው የጦር መሣሪያ በመሆኑ ከውጪ የሚገኘው ምንዛሬ ለዚህ ጠቃሚ ሳልሆነ ነገር ሳይ በከንቱ እንዲፈስ ተደርጓል ። ይህ መንግሥት እስካለ ድረስና የሀገሪቱ የውስጥ ኢኮኖሚ ተቀዋም እስካልተለወጠ ድረስ የውጪው ንግድ ሚዛን ይሻሻላል ማለት ዘበት ነው ።

ይህ 23ኛው ጠ/ጉባዔ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ሁኔታ በሰፊው ከመረመረ በኃላ የሚከተለውን ውሳኔ አሳልፏል ።

1ኛ ዛሬ በሀገራችን ለሰፈነው ትልቅ ወቅታዊ የኢኮኖሚ ችግር የአሁኑ መንግሥት ዋና ተጠያቂ እንደሆነ ያምናል ።

2ኛ በየጊዜው የወጡት የዘመቻ ፕሮግራሞችና የኢኮኖሚ ዕቅዶች ሰፊውን ሕዝብ ለመደለያና እንዲያው ለይስሙላ የወጡ ናቸው፡፡በመሆኑም እስካሁን ድረስ ፋርስ መሆናቸውን አስመስክረዋል ።



3ኛ የሚወጡት ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ደግሞ የሀገሪቱን ሁኔታ በትክክል የሚያንፀባርቁ ያልሆኑ፣ የሀገሪቱን ችግሮች ሊፈቱ የማይችሉና አሁንም ሲሆን የዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም በደነገገው ዕቅድ መሠረት የሚወጡ በመሆናቸውና የምሥራቅ አውሮፖ ሀገሮችም በዚህ ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ስለሆነ፣

4ኛ ከዚህ በተረፈ ይህ መንግሥት የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ችግሮች "ለመፍታት" የሚመካው በቢሮክራሲው፣ በቴክኖክራቶችና በውጪ ኃይሎች ላይ በመሆኑ፣ ይህም ከፀረ– ዲሞክራቲክነት ጠባዩ አንዱ ስለሆነ፣

5ኛ ከዚህም በመነሳት፣ የአንዱ ሀገር ኢኮኖሚ እድገት የሰፊውን ሕዝብ ፍላጎት ሊያሟላ የሚችለው በሀገሪቱ ውስጥ ሰላም የሰፈነና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የተረጋገጠ እንደሆነ ብቻ በመሆኑ፣

6ኛ የዛሬውን ጊዜያዊና የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ ችግር መፍታት የሚቻለው የአሁኑን አገዛዝ ደምስሶ ዲሞክራቲክ ሥርዓት ሲመሰረት ብቻ ስለሆነ፣ በኢትዮጵያ ውስጥና በውጪ የሚታገሉ ዲሞክራቲክና ተራማጅ ኃይሎች በዛሬው አገዛዝና ግብረአበሮቹ ላይ የጋራ ክንዳቸውን እንዲያነሱ ይህ ጉባዔ በድጋሚ የሀገር ፍቅር የተሞላበትን ጥሪውን ያቀርብላቸዋል ።

## የማኅበራዊ ጉዳይ ሁኔታ

ዛሬ የሀገሪቱ የማኅበራዊ ሁኔታ መበላሸት የኢኮኖሚው መዳቀቅና መዘበራረቅ ነፀብራቅ እንደሆነ ለመገመት አያዳግትም ። የኢኮኖሚ ማደግና መበላሸት እንደዚሁ ለማኅበራዊ ሁኔታ በጥሩ መልክ ለመገኘትና ለመበላሸት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላለው ሁለቱን መነጣጠል ያስቸግራል ። ሁለቱም የአንድ ሳንቲም ገጽታዎች ናቸው ።

በሀገራችን የሰፈነው ኢኮኖሚያዊ መዘበራረቅና መዳሸቅ ብዙ በሥራ ሊሰማሩ የሚችሉ ኃይሎችን ጠቃሚ / ፕሮዳክቲቭ / በሆነ ሥራ ላይ እንዳይሠማሩ አድርጓል ። ምንም የገቢ ምንጭ የሌለው የግዴታ የዕለት ኑሮውን ለማሸነፍ ቢል በሌላ ሥራ ላይ መሰማራት ስለአለበት፣ ዛሬ ከቀድሞ በባሰ ሁኔታ ፡በትላልቅ ከተሞች ውስጥ፣ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በድብቅ ሥራ አጥነት የሚሰቃዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ወደ ሌሎች የነፍስ ማዳኛ መስኮች ተሰማርተዋል ። በመሆኑም ለማኝነት፣ ሌብነት፣ ማጅራት መቺነት ተስፋፍተው ሲገኙ፤ በዚህ መስክ ያልተሰማራው ደግሞ በሌሎች በጣም ዝቅተኛ ገቢ በሚያስገኙ ዘርፎች ላይ በመሰማራት በድኅነት እየማቀቀ ነው ።ሌላውም በዚህም በዚያም ብሎ ሥራ ለማግኘት ያልቻለው የሥራ አጥ ሕዝብ ቁጥሩን እየቆጠረ በመኖር ላይ ነው ።

ከዚህ በተረፈ፣ ሥራ ለማግኘት የማይችሉ እህቶቻችን በሴተኛ አዳሪነት ሥራ እንዲተዳደሩ ተገደዋል ። ኢትዮጵያችን አሁንም እንደወትሮው በሴተኛ አዳሪ ብዛት በዓለም ውስጥ የበላይነትን ከያዙት ሀገሮች አንዷ ነች ። ይህም ተዘዋዋሪና ቋሚ ሴተኛ አዳሪ የሚባል ስም በማግኘት ትልቅ ሪኩን የቻለ የሥራ መደብ ሆኗል ።

ሌላውን ተማሪ ወጣት በሚመለከት ፣ በኩል፣ በትምህርት ቤት ጥበት ምክንያት በቀን ውስጥ ሁለት ሰዓት ብቻ እንዲማሩ በመገደዳቸው፣ አብዛኛው ወጣት ጊዜውን በሻይ ቤት በማባለፍ፣ ዕፅ አጫሽ በመሆን ፣ በመዘር ...ወዘተ ይህ አዲስና ለጋ ትውልድ ሊማር፣ ሊያስብ፣ ሊመራመር የሚችልበትን ጊዜ በከንቱ እንዲያባክን ተገዷል ።



ዛሬ በሀገራችን ላይ አሳዛኝ ሆኖ የሚታየው ሁኔታ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የለማኝ ቁጥር መብዛቱ ነው ። በተለይም ለጦርነት ተማገደ አጅና አገሩን ተቆርጦ የመጣውና ሌላም ከባላገር ችግር እያፈናቀለ ወደ ከተማ እንዲሸሽ የተገደደው ደካማ የኅብረተሰብ ክፍል በዚህ ለሰው ልጅ የማይገባ መስክ ላይ እንዲሰማራ ተገዷል ። የዛሬው አገዛዝ ልክ እንደ ቀድሞ ኃይለሥላሴ አረመኔ መንግሥት፣ የሚያደርገው ድርጊት እንደጠበታ ውኃ ይመሳሰላል ። ትላልቅ የውጪ ሀገር ሹማምንት ሲመጡና የዓለም አቀፍ ድርጅት ስብሰባዎች በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሲካሄዱ ለማኞቹ ከከተማ እየተለቀሙ ወደ ሌላ ቦታ እንደሚወሰዱ የአደባባይ ምስጢር ነው ።

በሀገራችን የተፈጠረው አሳዛኝ የማኅበራዊ ሁኔታ ከላይ በተጠቀሱት የማኅበራዊ ችግሮች ላይ ብቻ ያተኮረ አይደለም ። ሰፊ የመኖሪያ ቤት እጥረት ከመኖሩ የተነሳ ብዙ ሰው በአንድ ቤት ውስጥ እየተደረደረ እንዲኖር ተገዷል ።ይህ ሁኔታ ደግሞ በዚያች የሕክምናና የጤንነት ጉድለት፣ የተባይ ብዛት በሚወራጭበት ሀገር ሕዝቡን ወደ ሌላ በሽታ ውስጥ እንደሚጥለው የታወቀ ነው ። የሕክምናን ሁኔታ የተመለከትን እንደሆነም፣ ሀገሪቱ በሀኪም ቤቶች እጥረት፣ በበቂው ሀኪም አለመኖር የታማሚውን ሕዝብ ጥያቄ በፍጹም ልታሟላ አልቻለችም ። በተለይም ዛሬ፣ ብዙ ሕዝብ በረሃብ ምክንያት የተነሳ በበሽታ በሚሰቃይበት ወቅት ያለው መንግሥት የአጭር ጊዜ ፕሮግራም አውጥቶ ለጊዜያዊ ችግር መፍትሔ መፈለግ በሚያሻበት ወቅት ሁኔታዎችን አድፍጦ በመመልከት ላይ ይገኛል ።

በእውነቱ የሀገራችን ማኅበራዊ ችግር ጥልቅ ነው ። ለችግሩ መሻሻልና መወገዱ የግዴታ የኢኮኖሚው ሁኔታ መልክ መያዝ አለበት ። ለዚህ ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ ሰላምና ዲሞክራሲ መስፈን አለባቸው ። ለእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ መፈጠር ደግሞ የግዴታ የአሁኑ መንግሥት መደምሰስ አለበት ብሎ ይህ ጉባዔ ያምናል ።

## የግንባር ጥያቄ

የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ተወዳዳሪ በማይገኝለት ጨካኝ፣ አረመኔ፣ ፀረ–ሕዝብ አምባገነንና አሻንጉሊት መንግሥት ሥር ፍዳቸውን እያዩ ለመሆኑ የታወቀ ነገር ነው ። የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብታቸው ተገፎ፣ ብሔራዊ ነጻነታቸው ተደፍሮ ይገኛል ።

ይህ ከሃዲና ትምክህተኛ መንግሥት ባለፉት ዓመታት ውስጥ በጠመንጃ አፈሙዝና በዓለም አቀፍአዊነት ስም በሚነግዱ ተስፋፊው የሶቭየት ኅብረት መንግሥትና ገብረአበሮቹ እየተረዳ በሥልጣን ኮርቻ ላይ ተደላድሎ የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝቦች በአሰቃቂ ችግር ውስጥ እንዲቆሉ አድርጓቸዋል ። የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ፍትህን፣ የዲሞክራሲ መብትንና ብሔራዊ ነጻነትን ለማስከበር ያካሄዱትንና የሚያካሂዱትን መራራ ትግል በማፈን፣ በብዙ መስዋዕትነት የተገኙትን አብዮታዊ ድሎች ቀልብሶ መላ ሀገሪቱን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ቀውስ ውስጥ ከቷታል ። ይህ ትምክህተኛና ፋሽሽት መንግሥት እምነቱን በተስፋፊ የውጪ ኃይል ትከሻ ላይ ከጣለ በኋላ ለዲሞክራሲና ለእኩልነት በሚታገሉ ኃይሎች ላይ በሙሉ ፋሽሽታዊ ጭፍጨፋ በማካሄድ ላይ ይገኛል ።

የሩሲያ ተስፋፊ መንግሥት አሻንጉሊቱን የወታደር መንግሥት በሥልጣን ኮርቻ ላይ አቅፎ ደግፎ ይዞ፣ በሀገሪቱ ውስጥ በየቦታው የእርስ በእርስ ጦርነት እንዲጧርና እንዲፋፋም በማድረግ፣ በገፍ የሚያመርተውን የጦር መሣሪያ በማራገፍ፣ የሀገሪቱ ሀብት እየዘረፈና የሰፊው ሕዝብ ደም በከንቱ እንዲፈስ እያደረገ ነው ።

ይህንን ትምክህተኛና አድኃሪ ጦርነት በመቃወም በየቦታው እንቅስቃሴ ቢኖርም፣ በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ ጉልቶ የሚታየው የብሔር/ብሔረሰቦች ለመብታቸው የሚያደርጉት ትግል ነው ። ትምክህተኛው መንግሥት የጭቁን ብሔር/ብሔረሰቦች መብት በመርገጥ በሚያደርገው የጭፍን ጭፍጨፋ ተቆጥቶ፣ ይህን ጭቆናና ጭፍጨፋ ለመቋቋም በዱር በገደል ተሰማርቶ የጠበንጃ ትግል የማያካሂድ የብሔር/ብሔረሰብ እንቅስቃሴ የለም ። የዛሬው ጭቆና መረን የለቀቀ በመሆኑ፣ የብሔሮች ጥያቄ በሚደረገው ውጣ



ውረድ የበዛበት ትግል ውስጥ ከፍተኛ ሚናን እየተጫወተ መጥቷል ።

ምንም እንኳን የብሔር/ብሔረሰቦች ትግል ጉልቶ ቢታይም ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችና መደቦች የሚያደርጉት ትግል የሚናቅ አይደለም ። ወዝአደሩ፣ አርሶ አደሩ፣ ወታደሩ፣ ምሁሩ፣ ወጣቱ፣ ሴቱ፣ ...ወዘተ በየፊናው በተለያየ መንገድና ዘዴ ተቃውሞውን እያሰማ ነው ። በእነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ በቀይ ሽብር ስም የተካሄደው አረመኔአዊና ፋሽሽታዊ ጭፍጨፋ ትግላቸውን ለጊዜው ቢያዳክመውም፣ እንቅስቃሴው እየተፋፋመና እያደገ በመምጣት ላይ ይገኛል ። ያለፈው ጭፍጨፋ ያደረሰውን ጉዳት በመመልከትና ጭቆናው በቀላሉ የማያፈናፍን በመሆኑ፣ ትግሉ ትዕግሥትንና ጊዜን የሚጠይቅ መሆኑን ታጋዮች ተረድተው የህቡዕ ትግል ልምዱን በማድረግ በየፊናውና በየሥራ መስኩ እየተደራጁና እየታገሉ ነው ።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት ሰፊው ሕዝብ የሚወርድበትን አመጽና ግፍ ለመቋቋም እንደየሁኔታው ከዳር እስከ ዳር መነሳቱን እናያለን ። ሆኖም፣ ይህ ትግል ያልተቀነባበረና ተናጠል በመሆኑ፣ አምባገነኑ መንግሥትና ገብረአበሮቹን ለመጣልና በሀገሪቱ ውስጥ ሰላምና ዲሞክራሲን ለማስፈን የሚቻለው፣ ትግሉ ከተናጠል ትግል ወደ ተቀነባበረና የአንድነት ትግል ያመራ እንደሆነ ብቻ መሆኑን በመገንዘብ፣ ዛሬ የወቅቱ አጣዳፊና አንገብጋቢ ጥያቄ ይህን ተበታትና የሚገኝ የሕዝብ ትግል ማስተባበርና የጋራ ጠላትን በተባበረ ክንድ መጣል ነው ።

በአውሮፖ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር 23ኛ ጠ/ጉባዔ ከላይ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ከመረመረ በኋላ የሚከተሉትን ውሳኔዎች አሳልፏል ።

1ኛ ማኅበራችን፣ ብሔር/ብሔረሰቦችን የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ለመወሰን እስከመገንጠል ድረስ ያላቸውን መብትና ለዚህም የሚያደርጉትን ትግል እያወቀ፣ እነዚህ ድርጅቶች ከዚህ ባሻገር በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ያለውን ሁኔታ በመገንዘብና የጋራ ግንባር አስፈላጊነትን በመረዳት፣ ነጻነት፣ ለገለልተኛ ፖሊሲና [illegible]

ሆች ከሚታገሉ ከማንኛውም አገር አቀፍ ድርጅቶች ጋር የጋራ ግንባር ለመመሥረት ከፍተኛ ጥረት እንዲያደርጉ ጥሪውን ያቀርባል ::

2ኛ ከዚህ በመነሳት በሀበሶ የሚታገሉ መኢሶንና ሌሎች ሀገር አቀፍ ተራማጅ ድርጅቶች ታሪክ የጣለባቸውን ኃላፊነት በመገንዘብ፣ ለዚህ የጋራ ግንባር መመስረት ከፍተኛ ጥረት እንዲያደርጉ ይሄ ጉባዔ መልዕክቱን እያስተላለፈ፣ በሚያደርጉት ጥረትና ትግል ማንኛውንም አቅሙ የፈቀደለትን የማቴሪያልም ሆነ የፖለቲካና የሞራል ድጋፍ በመስጠት ትብብሩን የሚገልጽ መሆኑን ያስታውቃል ::

3ኛ በውጭ ሀገር የሚገኙ የብሔር/ብሔረሰብ እንቅስቃሴዎች፣ ሌሎች ሀገር አቀፍ ድርጅቶችና የተማሪ ማኅበራት፣ የወታደሩን አገዛዝና የሩሲያን ተስፋፊ መንግሥት የሚያደርጉትን ወንጀል፣ በዓለም ሕዝብ ፊት በመተባበር እንዲያጋልጡና በሀገር ቤትም ለጋራ ግምባር መመሥረት ለሚካሄደው ትግል አስተዋጽኦ ያበረክቱ ዘንድ፣ ለዚህ የጋራ ድርጊት አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስዱ ጉባዔው ጥሪውን ያቀርባል ::



## ስ ለ ረ ሃ ብ

መቼም የፖለቲካ ቀውስ ባለበት ሀገር የኢኮኖሚ ቀውስም እንደሚኖር በገሃድ የታወቀ ጉዳይ ነው ::

በቀደሞው የኃይለሥላሴ አገዛዝ ሥር የኢትዮጵያ ሕዝቦች ያሳዩት ወይም ያልቀመሱት የስቃይ ዓይነት አልነበረም የ1973ቱ ረሃብ ከ200 000 በላይ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሕይወት ይዞ አልፏል ::

በአሁኑ ጊዜ በዜና ማሰራጫዎችና በአገር ውስጥ በድብቅና በገልጽ ከተነሱ ፊልሞች ለመረዳት እንደሚቻለው፣ ከ1973ቱ የረሃብ ጊዜ የከፋ ሁኔታ እንዳለ ነው :: በመሆኑም፣ ኢሲተማ በ23ኛው ጠ/ ጉባዔ ላይ ስለዚህ ጉዳይ አባባቢነት በሰፊው ከተወያየ በኋላ፣ ምንም እንኳ ለጊዜው ዝናብ ባይዘንብና በዚህም ምክንያት ድርቅ ቢገባም፣ ለዚህ ረሃብ ዋና ተጠያቂ የአሁኑ ፈላጭ ቆራጭ መንግሥት መሆኑን በጥብቅ ይገነዘባል ::

ድርቅ የገባባቸውን቉ በታዎችና በረሃብ የተጠቁ ክፍለሀገሮችን ስንመለከት አብዛኛው ክፍል በ1973ቱ ዓ.ም የተነካው ቦታ ነው :: ሆኖም በጊዜው ስለዚህ ጉዳይ ተጠንተው የቀረቡትን የድርቅ መከላከያ ዘዴዎች የወታደሩ መንግሥት ችላ በማለት በጊዜው አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ አልፈለገም :: እንዲያውም፣ ሁኔታውን ችል ከማለቱ የተነሳና የሰፊውን ሕዝብ ትግል ለማፈን ባለው ፍላጎት መሠረት በአራትም ማዕዘን የሚያካሂደው ትምክህተኛ ጦርነት ሁኔታውን አባብሶታል ::

ዛሬ የሀገሪቱ የእርሻና የኢንዱስትሪ ምርት ውጤቶች ለዚህ ሕዝብ አስጨራሽ ጦርነት የሚውሉ እንጂ፣ የተራበውን ሕዝብ ከስቃይ አፋፍ ላይ ለመመለስ የሚደረገው ጥረት በጋለ ድንጋይ ላይ የሚደረግ የውኃ ጠብታ ሆኗል :: ይባስ ብሎ፣ በዓለም ላይ ከሚገኙ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ሌሎች ዕርዳታ ለጋሽ ድርጅቶችና መንግሥታት የሚገኘውን እህልና ሌሎች የሕክምናና የልብስ ዕርዳታዎች ለተራበው ሕዝብ ከማድረስ ይልቅ በየቦታው ለሠፈረው ወታደር ቀለብ እንዲሆን በመደረግ ላይ ነው ::

የ23ኛው የአኢተማ ጠ/ጉባዔ ይህንን ከመረመረና ከተወያየበት በኋላ

ሀ/ ከውጭ የሚመጣው ዕርዳታ በቀጥታ ለተራበው ሕዝብ እንዲደርስ ለዕርዳታ ሰጪዎች በየጊዜው ጥሪውን ያቀርባል ::ለዚህም ቁጥጥር እንዲያደርጉ ያስገነዝባል ::

ለ/ በውጭ አገር የሚገኙ የተደራጁም ሆነ ያልተደራጁ ኢትዮጵያውያን ከሐይማኖት፣ ከርዕዮተዓለምና ከሌላ የፖለቲካ እምነት ባሻገር ለተራበዉ ወገናችን በጋራ እንድርስለት ዘንዱ ጥሪውን ያስተላልፋል ::

THE ETHIOPIAN STUDENTS' UNION IN EUROPE